በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No 1/202/10
ቀን / Date 05 ጳጒሜ 2010

በዝርዝሩ ለተመለከቱት
በያሉበት

ጉዳዩ:- ሰርኩላር ማስተላለፍን ይመለከታል፤

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በሚመለከት ከአሁን በፊት የወጡ መመሪያዎችን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ማሻሻያውን ከዚህ ጋር በማያያዝ የላክን መሆኑን አሳስባለሁ።

"ከሠላምታ ጋር"

ሙሴ ሁሴን አባ
ዳይሬክተር /ሚኒስትር

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን !!
ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559

በዝርዝሩ ለተመለከቱት

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምን ይመለከታል፤</u>

ስለሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም በወጣው ደንብ ቁጥር 139/99 አንቀጽ 3 መሠረት ባለሥልጣኑ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለባቸውን ግብር ከፋዮች ዝርዝር ያወጣ ቢሆንም በዝርዝሩ ከተመለከቱት ግብር ከፋዮች መካከል የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም የማያስፈልጋቸው መኖራቸው ታውቋል፡፡

ስለሆነም ባለሥልጣኑ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ስለመጠቀም ያወጣውን የተጠቃሚዎች ዝርዝር እንደሚከተለው አሻሽሏል፡፡

1. ማንኛውም የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ለሚያከናውነው ግብይት ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የወጣ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
2. የሚከተሉት የሽያጭ መመዝገቢይ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ የለባቸውም፡፡
   ሀ) ከ500,000 ብር በታች ዓመታዊ ገቢ ያላቸው ድርጅቶችና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች፤
   ለ) የቤት ኪራይ ገቢ የሚያገኙ ግብር ከፋዮች፤
   ሐ) ጠበቆችና/ወይም አማካሪዎች፤
   መ) ሳኪዎች፤
   ሠ) ሥዕል ወይም የቅርፃ ቅርጽ ሥራ የሚሰሩ ግብር ከፋዮች፤
   ረ) የአምቡላንስ አገልግሎት የሚሰጡ ግብር ከፋዮች፤
   ሰ) የቤት ለቤት ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ግብር ከፋዮች፤
   ሸ) በእርሻ ሥራ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች፤

ቀ) ለብሔራዊ ባንክ ወርቅ የሚያቀርቡ ግብር ከፍዮች፤

በ) በምርት ገበያ ማዕከል በኩል የሚገበያዩ ግብር ከፋዮች፤

3. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 2 የተመለከቱት ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢይ መሣሪያ ባይጠቀሙም የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ከሆነ በመመሪያ ቁጥር 110/2008 መሠረት በባለሥልጣኑ ፈቃድ ደረሰኝ በማሳተም የመጠቀም ግዴታ አለባቸው።
4. የደረጃ (ሐ) ግብር ከፋይ ሆኖ በፈቃደኝነት የሚሐሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም በመመሪያ ቁጥር 110/2008 መሠረት በባለሥልጣኑ ፈቃድ የታተመ ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ ይኖርበታል።
5. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ማንኛውም ግብር ከፋይ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው አገልግሎት በማይሰጥበት ጊዜ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የታተመ ደረሰኝ የመጠቀም ግዴታ ይኖርበታል።
6. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሲጠቀሙ የነበሩና በዚህ ሰርኩላር መሠረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ የሌለባቸው ግብር ከፋዮች ለባለሥልጣኑ በማሳወቅ በአወጋገድ መመሪያ ቁጥር 114/2008 መሠረት መሣሪያውን ማስወገድ ይኖርባቸዋል። ሆኖም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በሚወገዱበት ጊዜ በመሣሪያዎቹ ውስጥ የሚገኘው መረጃ በሙሉ ወደ ባለሥልጣኑ የመጃ ቋት (ሰርቨር) መላኩ መረጋገጥ ይኖርበታል።

በመሆኑም በዝርዝሩ የተመለከታችሁ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ ይህ ሰርኩላር ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በሰርኩላሩ መሠረት እንዲፈፀም እንደታደርጉ አሳስባለሁ።

"ከሠላምታ ጋር"

[signature] ሁሴን እባ
ዋና ዳይሬክተር /ሚኒስትር

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለአቅም ግንባታና የሀብት አስተዳደር ዘርፍ
- ለሕግ ማስከበር ዘርፍ
- ለአገር ውስጥ ታክስ ዘርፍ
- ለጉምሩክ ዘርፍ
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ አስ/ማጣጣምና የክልሎች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

<u>የኢ/ገ/ጉ/ባለሥልጣን</u>